# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 308 መጋቢት 26 2006


ያልተዘራ አይታጨድም። ወያኔ የዘራልን መርዝ የሚያፈራው መርዝን እንጂ ሌላ አይደለም። ልዩነቶቻችን እንደዘመኑ በሰለጠነ ዲሞክራሲያዊ መንገድ እንጂ በተያዘው መንገድ ማስወገድ አይቻልም። በመሆኑም ለመከፋፈል ከመመቻቸት ይልቅ አንድነታችን በማጥበቅ የነጻነት ሃይሎችን በመቀላቀል ራሳችን እና የሀገራችንን ህልውና ከዚህ ከወያኔ የመከፋፈል መርዝ እንታደግ።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ወያኔ በእምነት ተቋማት ላይ ጣልቃ መግባቱን አጠንክሮ ገፍቶበታል

በሰላማዊነታቸውና፤ በእንግዳ ተቀባይነታቸዉና ለሌላ እምነት ተከታዮች ባላቸዉ ክብር ተወዳዳሪ የሌላቸዉን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች በአክራሪነትና በአሸባሪነት በመፈረጅ እንዲሁም ድምጻችን ይሰማ ብለዉ የጮሁ የእምነቱን ተከታዮች በመግደል፤ በማሰርና በማንገላታት የስልጣን ዘመኑን የማራዘም ዉጣ ዉረድ ዉስጥ የተዘፈቀዉ ፋሽስቱ ወያኔ ከሰሞኑ አይኑን ወደ ታሪካዊቷ የኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን በማዞር "ማህበረ ቅዱሳን" አሸባሪ ብሎ በመፈረጅ የጭቃ ጅራፉን ማጮህ ጀምሯል።

ከአወልያ ተነስቶ በመላው አገሪቱና በውጭ አገሮችም በሚገኙ የእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ሙሉ ድጋፍ ያገኘውን የእምነት ነፃነት ጥያቄ በጥይትና በጉልበት እፈታዋለሁ ብሎ በወሰደዉ ፋሺስታዊ እርምጃ አዲስ አበባና አርሲ ገደብ አሳሳ ዉስጥ የንፁሃንን ህይወት መቅጠፉ የሚታወቅ ሲሆን በሺህ በሚቆጠሩ ለእምነታቸው መደፈር ዘብ የቆሙ ሙስሊሞችን በልዩ ልዩ እስር ቤቶች በማጎር የማሰቃየት ተግባር እየፈፀመ ይገኛል።

ይህ አልበቃ ያለው ፋሽስቱ ወያኔ በማናለብኝነት እብሪት ተወጥሮ በኦርቶዶክስ እምነት ላይም በርካታ ሸፍጦችን መፈጸሙ የሚታወቅ ሲሆን ለአብነትም በዋልድባ ቅዱሱን ስፍራ አትረሱ ያሉ መነኮሳትን የደበደበ፤ ያሰረና ያፈላቀለ የባንዳ አገዛዝ ዛሬ ለክርስት እምነት ተቆርቋሪ በመምሰል ዳግም የጥፋት እጁን ወደ ቤተ እምነቱ በመሰንዘር ማህበረ ቅዱሳንን ለመምታት ዘመቻ መጀመሩ በበርካታ የእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ትዝብት ላይ የጣለው ሲሆን ዘመቻው በተለይም የማኅበሩ አመራርና አባላቱ ላይ ማነጣጠሩ ታውቋል። በቅርቡም የፋሽስቱ ወያኔ ልሳን በሆነው ቴሌቪዥን ማህበሩን፡ አመራርና አባላቱን ለውንጀላ የሚያመቻች በፈጠራ ድርሰት የታጀበ የዶክመንታሪይ ድራማ በመስራት ለመልቀቅ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን የውስጥ ምንጮቻችን አድርሰውናል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ሕወሃት የምርጫ ብድር እያደለ መሆኑ ተሰማ

በማጭበርበር፣ በማስፈራራትና በመደለል የአገዛዙን ወንበር ከሚይዝ በቀር አንድም ጊዜ የፖለቲካ አማራጭ ሆኖ ቀርቦ የማያውቀው ወያኔ ለቀጣዩ ዓመት ምርጫ ከተለመደው የማጭበርበር ስራው ዝግጅት በተጨማሪ ዳጎስ ያለ የገንዘብ ችሮታ በብድር ስም እያደለ መሆኑ ተሰማ። በጎንደርና በሌሎችም የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚኖሩ አርሶአደሮችን፣ ስራ አጥ ወጣቶችንና እናቶችን ሳይቀር እንደጨመረ የተነገረለት ይህ የቀጣዩን ዓመት ምርጫ ታሳቢ ያደረገ ብድር በሶስት ዓመት ውስጥ ተመላሽ እንደሚሆንም አብሮ የደረሰን መረጃ ያረጋግጣል።

በግለሰብ ደረጃ ራሳቸውን በሙያ አንጸው፣ በመሃበር ተደራጅተውና የተለያዩ ማህበራዊ ችግሮችን ሊቀርፉ የሚችሉ የስራ አማራጮችንና የስራ እቅዳቸውን ጭምር አስተካክለው አቅርበው የወያኔ አባል ባለመሆናቸው ብቻ ምንም አይነት እገዛ እንደማያገኙ የተነግራቸውና የተባረሩ ሁሉ በዚህኛው የወያኔ እቅድ ሊካተቱ መቻላቸው ሁሉንም ያስገረመ ሆኗል ተብሏል። ከዚህ በፊት ተደርጎ በማያውቅ ሁኔታ በየአካባቢውና በየቤቱ እየተኬደ ወጣቶችንና የሚመለከታቸውን ሁሉ ለብድሩ እንዲመጡ መጋበዝ ከሕወሃት መራሹ ወያኔ ያልተለመደና ከኋላው አንዳች ነገር እንዳለ የሚያመለክት ነው የሚሉ አንዳንድ ታዛቢዎች መጨረሻው የሚያምር አይመስለንም ያላሉ።

ፋሽስት ወያኔ ከዚህ በፊት በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተሞች በተለያዩ ምክንያቶች የሰጠውን ብድር በማስመለሱ ሂደት በጊዜው መክፈል ላልቻሉ ወገኖቻችን የመክፈያ ጊዜውን በማራዘም ፋንታ በእጅ ያለን አንጡራ ሃብት እስከማሸጥ መድረሱና በተለይም ለተበዳሪዎች ብቻ ሳይሆን በስራቸው ለሚተዳደሩ የቤተሰቡ አባላትም እጅግ አሰቃቂ እና ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## የትምህርት ጥራት መውደቅ ለተማሪው ተስፋ መቁረጥ አይነተኛ ምክንያት እንደሆነ ተጠቆመ

መሟላት የሚገባቸው መማሪያ መጽሃፍትን ጨምሮ ሌሎችም የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ሳይሟሉ፣ የመምህራን ብዛትና ጥራት ሳይስተካከል፣ የመማሪያ ክፍሎችና ወንበሮች የተማሪውን ብዛት አገናዝበው ሳይገነቡና ባንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩት ተማሪዎች ብዛት አስተማሪው ፍጹም ሊቆጣጠረው ከሚችለው በላይ ባለበት ሁኔታ በኢኮኖሚ እጅግ ካደጉ ሀገሮች በቀጥታ የተቀዳና የተተገበረው የመማር ማስተማር ሂደት የትምህርት ጥራቱን እጅጉን እንደጎዳው በተማሪዎች፣ ባስተማሪዎች፣ በወላጆችና ጉዳዩ በሚመለከታቸው ሌሎች አካላትም በሰፊው ይነገራል።

አንዳንድ ታዛቢዎች እንደሚሉት ደግሞ ሕወሃት ባለፉት የአገዛዝ ዘመኖቹ የትምህርት ስርአቱን በማሻሻል የትምህርት ጥራትን ለማምጣት ሞክሪያለሁ ቢልም መጀመሪያውኑ በተሳሳተ አመለካከትና የትምህርት አሰጣጥ መንገድ ላይ የቆመ ስለነበር የተሻለ ነገር ሊፈጥር አልቻለም፤ መሰረቱ ትክክል አልነበረም እና። ችግሩን በተመለከተም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት በተለይም ከመምህራን አካባቢ ብዙ ማሳሰቢያዎችና ማስጠንቀቂያዎች ቢሰነዘሩም ሁሉንም እኔ አውቃለሁ የሚለው ሕወሃት መራሹ ወያኔ ሊቀበል በለመቻሉ አሁን ከለንበት እጅግ አሳፋሪ የትምህርት ጥራት ላይ ልንገኝ ችለናል ይላሉ።

የፌዝ በሚመስልና የውስጣቸውን ንዴት ድምጻቸው በሚያሳብቅ ምልኩ አስተያየታቸውን የሰጡት ደግሞ "ከ11ኛ ክፍል ባንዴ ዘለው የሁለተኛ ዲግሪ ባለቤት መሆናቸውን የሚገልጽ ማረጋገጫ በማቅረብ ሀገር እየመራን ነው ሲሉ የሚያዩና የሚሰሙ ተማሪዎቻችን ያሉበትን ደረጃ ኮርጀውም ሆነ አጭበርብረው ለማለፍ ቢሞክሩ ነውር ይሆን ይሆን? መስራት ሳይሆን በስረቅ በሚያስመሰግንበት የወያኔ ስርአት ተወልደው ያደጉት ልጆቻችን፣ አንዳንዶች ከክራይ ቤት ባንድ ጊዜ የባለ ሁለት እና ሶስት ሕንጻ በለቤት ሲሆኑ በእድሜያቸው ቆመው ያዩት የሕወሃት አገዛዝ ዘመን ልጆቻችን፤ "የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው" ዋናው ይዞ መገኘት ነው ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የወያኔ ወታደሮች በቦዲ ብሄረሰብ አባላት ላይ ተኩስ ከፍተዉ ብዙ ሰዎችን አቆሰሉ

የወያኔ የቆሸሸ ስርዐት በሚከተለዉ ዘረኛ ፖለሲ የተነሳ ደቡብ ኢትዮጵያ ዉስጥ በቦዲዎችና በኮንሶዎች መካከል ከአንድ ወር በላይ የዘለቀዉን የእርስ በእርስ ግጭት አበርዳለሁ በሚል ወደ አካባቢዉ የተጓዙ የወያኔ መከላከለያ ሠራዊት አባላት በቦዲዎች ላይ የከባድ መሳሪያ ተኩስ ከፍተዉ ሴቶችን፤ህጻናትንና አረጋዉያንን ጨምሮ ብዙ ሰዎችን ማቁሰላቸዉን ደቡብ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች ገለጹ። ዘጋቢዎቻችን ጂንካ ከተማ ዉስጥ የሚገኘዉን የኦሞ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ኅብረት ጽ/ቤት ዋቢ በማድረግ በላኩልን ዜና መሰረት የወያኔ ወታደሮች በቦዲ ብሄረሰብ አባላት ላይ ላይ በመትረጊስ የታገዘ ተኩስ በመክፈቱ በርካታ ነዋሪዎች መቁሰላቸውን ከእነዚህም ውስጥ 17 አሮጊቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች በደቡብ ሃና ጤና ጣቢያ በህክምና ላይ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል።

የመከላከያ ሰራዊቱ የወሰደውን እርምጃ ተከትሎ የሰላማጎ ወረዳ አስተዳዳሪና ምክትል አስተዳዳሪ በአንድ ወገን ሆነዉ ከወረዳዉ የጸጥታ ዘርፍ ሃላፊ ለሆነዉ ስጦታው ከተባለ ግለሰብ ጋር የተፋፋመ የቃላት ጦርነት ዉስጥ መግባታዉን ከወረዳዉ የሚደርሱን መረጃዎች ያመለክታሉ። የኮንሶ የአገር ሽማግሌዎች በበኩላቸው " ወደዚህ አካባቢ አምጥታችሁት ስታሰፍሩን ከህዝብ ጋር ተመካክረናል፣ ሰላም ነው ብላችሁ ቢሆንም፣ ከመጣን በሁዋላ ግን ለተደጋጋሚ ግጭት ተዳርገናል። ይህም ሆኖ ግችቶችን በጋራ በአገር ባህል መሰረት እየፈታንና እያስተናገድንለ ባለንበት ጊዜ ይህን አይነት አሰቃቂ እርምጃ መውሰድ ከእንግዲህ ወዲያ አብሮ ለመኖር ያለንን ተስፋ የሚያጨልመው" ነው በማለት መናገራቸውን ድርጅቱ ገልጿል።

በቦዲና ወደ አካባቢው ሄደው እንዲሰፍሩ በተደረጉት ኮንሶች መካከል በሚደርሰው ተደጋጋሚ ግጭት እስካሁን 4 ኮንሶዎችና 2 ቦዲዎች እንዲሁም አንድ ሾፌር ተገድለዋል። 3 ኮንሶችና 1 ፖሊስ ሲቆስሉ 72 ቤቶች መቃጠላቸውን፣ ሰውናርድበጊዮ መንደር ደግሞ 1 የማዳበሪያ መጋዘን ከነማዳበሪያዎቹ መቃጠሉን ድርጅቱ በላከው መረጃ አመልክቷል። በግጭቱ ሳቢያ ለተፈናቀሉ ኮንሶዎች እርዳታ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ያልዘሩትን ማጨድ ከቶ አይቻልም!!

የወያኔ መንግስት የኢትዮጵያን ብሄር ብሄረሰቦች አጋጭቶ በመካከላቸው ጥርጣሬና መፈራራት አንግሶና የታሪክ ጠባሳዎችን እንደ አዲስ በመጓጐጥ እያደማ ከፋፍሎ ለመግዛት ካለመታከት ያደረጋቸው ሙከራዎች ገና ፍሬ ባያፈሩም ቁጥቋጦዎቹ መብቀል ጀምረዋል። እዚህም እዚያም በካድሬዎች የውስጥ ለውስጥ ተልእኮ የሚለኮሱ እሳቶች መብለጭለጭ ጀምረዋል። ሌላው ቀርቶ በአንድ ብሄረሰብ መሃል ሳይቀር በከባቢ ልዩነቶች ብቻ መናቆሮችና መጋደሎች እያስተዋልን ነው። ሰሞኑን በጉጂና በቦረና ኦሮሞዎች መካከል የወያኔ ሎሌዎች በሚያበረታቱት አተካሮ የብዙ ወገኖቻችን ህይወት ጠፍቷል። ሰዎች ከኑሮአቸው ተፈናቅለዋል። ወያኔ እንደኳስ ጨዋታ ተመልካች ዳር ሆኖ ይመለከታል፤ ያጨብጭባል።

ሰሞኑን ባህርዳር ከተማ ውስጥ በተካሄደ የስፖርት ውድድር ላይ አሳፋሪ ክስተት ነበር። ለሰሚው የሚቀፍ ብልግና የተቀላቀለበት ስድብና ቁርቋሶ አይተናል። ከበስተጀርባ ሆነው ይህንን ለፍቅር ብቻ ሊውል የሚገባ የስፖርት ዝግጅት መርዝ ረጭተውበታል። ከዚህ ላቅ ያሉ የተንኮል ድግሶችም ተደግሰው ህዝብ ውስጥ በወያኔ ከተነዙ የመርዝ ቢልቃቶች ውስጥ ስራ ላይ ሳይውሉ ቀርተዋል።

ይህ በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ ዘር የሚዘራው ወያኔ ያልተከፋፈለ ህዝብ አይገዛልኝም በሚል ፍልስፍና እንደሆነ በተደጋጋሚ እያየን ነው። ሶማሌ ክልል ውስጥ በተቋቋሙ ልዩ ፖሊስ በሚል ስያሜ በሚጠሩ የመንግስት ሃይሎች ጥቃት ቁጥሩ እጅግ በርካታ የሆነ የኦሮሞ ማህበረሰብ ከኖረበት መሬት ተጠራርጎ እንዲወጣ ተደርጓል። ብዙዎቹ ተገድለዋል። ብዙ ደም መቃበት ተፈጥሯል። በየክልሉ ምስኪን የአማራ ገበሬዎችን መሬት ንብረት በመንጠቅ አከባቢውን ለቀው እንዲሄዱ አድርገዋል። መሄጃ የለንም ያሉትንም ቀጥቅጠው እንደገደሏቸው ሰሞኑን ከጅባትና ሜጫ አካባቢ ያሉ መረጃዎችን አይተናል።

እነዚህ በየቦታው የሚብለጨለጩ እሳቶች በዚህ ከቀጠሉ ሁላችንም ወደ ሚያቃጥልና የሚለበልብ የሰደድ እሳት ማደጉ አይቀርም። የወያኔ ባለሚሎች ካለምንም ይሉኝታና ማሰላሰል ይህንን እሳት እያራገቡ ይገኛሉ።

ይህንን አደገኛ አዝማሚያ በንጭጩ ማስወገድ የሚችለው ራሱ ህዝቡና የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ የነጻነት ሃይሎች ድምጽና ህብረት እንጂ የወያኔ መንግስት አይደለም። ስለዚህ ህዝቡ በተለይም ወጣቶች ከዚህ ወጥመድ ሰብረው እንዲወጡ ግንቦት 7 የነጻነት፤ የፍትህና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አጥብቆ ያሳስባል። ተመሳሳይ ተንኮሎችንም ማጋለጡን ይቀጥላል። የብሄርሰብ ልሂቃንም ይህንን መርዝ እንዲቋቋሙ፤ ይልቁንም ወያኔ እንዳይመቸው ይበልጥ መቀራረብና ፈተናውን በጋራ እንድንቋቋም ጥሪያችን በድጋሜ እናቀርባለን።

ያልተዘራ አይታጨድም። ወያኔ የዘራልን መርዝ የሚያፈራው መርዝን እንጂ ሌላ አይደለም። ልዩነቶቻችን እንደዘመኑ በሰለጠነ ዲሞክራሲያዊ መንገድ እንጂ በተያዘው መንገድ ማስወገድ አይቻልም።

ዞሮ ዞሮ በዚህ ሳይጣናዊ የወያኔ መሰሪ ሴራ ለምትፈስ ለእያንዳንዱ የደም ጠብታ ተጠያቂው የወያኔ ጉጅሌ መሆኑን አጥብቀን እናሳስባለን። በመሆኑም ለመከፋፈል ከመመቻቸት ይልቅ አንድነታችን በማጥበቅ የነጻነት ሃይሎችን በመቀላቀል ራሳችን እና የሀገራችንን ህልውና ከዚህ ከወያኔ የመከፋፈል መርዝ እንታደግ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

### ወያኔ በእምነት ተቋማት ላይ ጣልቃ መግባቱን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ዘጋቢያችን የተለያዩ ሶሻል ሚዲያዎችን ዋቢ በማድረግ እንዳደረሰን ማህበረ ቅዱሳን ላለፉት ሁለት አስርት አመታት ታሪኩ የሠራው ሥራ አባላቱ በመዋቅራዊ አሠራር ብቻ ሳይወሰኑ በተናጠልም ጭምር ቤተ ክርስቲያንን ለመቋቋም፣ ፋሽስቱ ወያኔ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የሚፈጸመውን ደባዎችን በማጋለጥ፣ ሕዝበ ክርስቲያኑንም በአስተውሎትና በመረጃ በታገዘ መንገድ በማንቃት ሰፊ መሠረት ያለው ማኀበራዊ – መንፈሳዊ አቅምና እሴት ፈጥሯል የሚሉ በርካታ አስተያየት ሰጭዎች በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ላይ በፋሽስቱ ወያኔ የተቃጡ አደጋዎችንና ቤተክርስቲያኒቱ የሀይማኖት-የለሽ ካድሬዎች መፈንጫና የአገዛዙ መሣርያ የማድረግ የጸረ-ሀይማኖቱ አገዛዝ ሴራዎችን ከመቀልበስ የዘለለ አንዳችም አክራሪ ሊያስብለው የሚችል ተግባር አልፈጸመም ሲሉ እየሞገቱ ይገኛሉ።

በተለይም ባለፉት ሁለት አስርት ዐመታት ከህዝበ ሙስሊሙ ባልተናነሰ መልኩ የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን በዚህ ፋሽስታዊ አገዛዝ ተደቁሳለች፣ ተበድላለች፣ በርካታ ቤተ እምነቶች ተቃጥለዋል፤ በርካታ አማኞቹም እንዲሰደዱ ተደረገዋል። ረጃጅም የፋሽስቱ ወያኔ እጆች በቤተክርስቲያኒቱ በነበሩት በርካታ የአስተዳደር ችግሮች፣ ሙስናዎችና በርካታ ፀያፍ ስራዎች ላይ ሁሉ አሉበት፡ በአጠቃላይ ቤተ እምነቷ በፋሽስቱ ወያኔ አገዛዙ ክፉኛ ቆስላለች። ስለሆነ ፋሽስቱ ወያኔ በፈጠረው የኃይማኖት ነፃነት እጦት ወይንም የእምነት ጣልቃ ገብነት ምክንያት የመከራና የሰቆቃ ዘመን ከመግፋት ለመብታችንና ለቅዱሱ እምነታችን ዘብ በመቆም ሁሉም ቤተ እምነት ነግ በኔ በማለት ሁላችንም በጋራ ይህንን የእምነት ጸር የሆነውን የፋሽስት ቡድን ወደ ከርሰ ማቃብሩ ለመክተት መነሳት አለብን።

### የትምህርት ጥራት መውደቅ ለተማሪው ተስፋ መቁረጥ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ብለው ወደ ኩረጃ እና ማጭበርበር ቢገቡ ማን ይሆን የሚወቀሰው? ለመሆኑ ወያኔ ይህን የትምህርት ስርአት ሲተገብር ማንን አማከሯል? ለጥያቄ የወጡ ተማሪዎችንም ሆነ መምህራንና ወላጆችን በምን አይነት ሁኔታ ነበር መልስ የመለሰላቸው? ታዲያ ይህን ሁሉ የአገዛዙን ግፍ ያዩና መሞከሪያ የሆኑት ተማሪዎቻችን ሞራላቸው ወደቀ። ተስፋቸው እንክትክት አለ። ስለሆነም ለማንበብ ለመስራትና ለመትጋት ሳይሆን እንደ ገዥዎቻችን ባቋራጭ ማለፍን፣ ያለድካም ማግኘትን ተመኙ። በመሆኑም ኩረጃው ሳይሆን የትምህርት ጥራቱን የገደለው በመጀመሪያ የወደቀውና የተማሪዎችን ተስፋ ያጠፋው በመሞት ላይ ያለው የትምህርት ጥራት ነው ኩረጃውን እያበረታታ ያለው" ይላሉ።

ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ጊዜያት ሲደመጡ እንደሚሰሙት ደግሞ ፋሽስት ወያኔ የሳይንቲስት ትምህርት ቤቶች እና ሌሎችንም ስሞች በመቀጠል ባንዲት ሀገር ውስት የተለያየ የትምህርት አሰጣጥ በመከተል የራሳችን ለሚሏቸው አካባቢዮች ፍጹም የተለየ የትምህርት ግብአትን በማቅረብ የተሻለ ብቃት ያላቸው ተማሪዎችን ለማፍራት ሙከራ ሲያደርጉ እንደቆዩና እያደረጉም እንደሆነ ያደባባይ ሚስጥር ነው።

አንድን ሀገር ለመግደል የትምህርት ስርአቷን ግደል የሚለውን መርህ አንግቦ የተነሳው ሕወሃት በአገዛዙ በቆየባቸው ያለፉት 23 ዓመታት ስማቸውን በቅጡ መጻፍ የማይችሉና የተለያዩ መጽሃፍትን አገናዝበው ጽሁፍ ማዘጋጀት የማይችሉ እየጠፉ ያሉ የዩኒቨርሲቴ ምሩቃንን በማምረት ላይ ነው። በተቃራኒው ግን የትምህርቱ ጥራት ጉድለቱ እያጠፋቸው ያሉ አእላፍ ወጣቶች የሚውሉበት ከሰላሳ በላይ የዩኒቨርሲቲ ሕንጻ ገነባው እያለ ሪፖርት እንደሚያቀርብ አይዘነጋም።

# ወያኔ እያለ በሰላም፤ እድገትና የህዝብ አንድነት ሊኖር አይችልም

ባለፉት ሁለት አስርተ አመታት በዲሞክራሲ ላይ ገንብተን የመሰረትነዉ ፌዴራሊዝም ልዩነታችንን ያቀፈ ስርአት መገንባት እንድንችል አድርጎናል። ይህ ጅምራችን ደግሞ በኢትዮጵያ ዉስጥ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦችን ማቀፍ የቻለ የመጀመሪያዉም የመጨረሻዉም የተሳካ ጅምር ነዉ ብለን እናምናለን። ይህ የፈጠርነዉ የፌዴራል ስርዐት ኢትዮጵያ ዉስጥ ብሄር ብሄረሰቦች ባህላቸዉና ቋንቋቸዉ ተከብሮ በማንነታቸዉ እየኮሩ ኢትዮጵያ የሚባል ማህበረሰብ እንዲመሰርቱ አስችለናል።

ይህ ከዚህ በላይ ያዳመጣችሁት አረፍተ ነገር መለስ ዜናዊ እንደ ፈረንጆቹ ዘመን አቆጣጠር በታህሳስ ወር 2010 ዓም አዲስ አበባ ዉስጥ በተዘጋጀዉ አምስተኛዉ አለም አቀፍ የፌዴራሊዝም ኮንፈረንስ ላይ ካደረገዉ ንግግር የተቀነጨበ ነዉ። መለስ ዜናዊ ከሞተ ሁለት አመት ሊሞላዉ በወራት የሚቆጠር ግዜ ነዉ የሚቀረዉ። ዉድ ጀግኖቿና የቁርጥ ቀን ልጆቿ ካልደረሱላት በቀር መለስ ዜናዊ በዲሞክራቲክ ፌዴራሊዝም ላይ ገነባናት ብሎ የተናገረላት ኢትዮጵያም ከወያኔ የተጋባባት ክፉ የዘረኝነት በሽታ ተጠናዉጧት ልትሞት የቀራት አንድ ሐሙስ ብቻ ነዉ።

ወያኔ በየአመቱ ህዳር ወር ላይ የፌዴራሊዝም ቀን እያለ የአገሪቱን ብሔር ብሄረሰቦች ሰብስቦ ሲያስጨፍር የተመለከተ ሰዉ እዉነትም የወያኔ ጎሳንና ቋንቋን ማዕከል ያደረገዉ ፌዴራሊዝም የኢትዮጵያን ብሄር ብሄረሰቦች ያቀራረበ ሊመስለዉ ይችላል። የወያኔም ፍላጎት አንዳንድ የዋሆች እንደዚህ አይነቱን የእዩልኝ ድራማ እየተመለከቱ ዋናዉን ጉዳይ እንዲረሱት ነዉና እነዚህ በግልጽ የሚታይ ወጥመድ ዉስጥ አይናቸዉን ጨፍነዉ የገቡ ሰዎች ወያኔ የፈጠረዉን ህዝብን ከህዝብ ጋር የሚያጋጭና የሚከፋፍል ስርዐት ቢያደንቁ ብዙ ሊገርመን አይገባም። ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች የፌዴራል ስርዐት ፈጥረን ብሄር ብሄረሰቦች እራሳቸዉን በራሳቸዉ እንዲያስተዳድሩና በሰላም አብረዉ እንዲኖሩ አድርገናል ብለዉ በተናገሩባቸዉ ባለፉት ሃያ ሁለት አመታት ኢትዮጵያ ዉስጥ በተለያዩ ብሄር በሄሰቦች መካከል የተፈጠሩትን ደም ያፋሰሱ አያሌ ግጭቶችን ረጋ ብሎ ለተመለከተና ላስተዋለ ሰዉ ግን ጉዳዩ ወዲህ ነዉ።

በመሰረቱ ኢትዮጵያን በመሳሰሉ ብዙ ብሄር ብሄረሰቦች ጎን ለጎን አብረዉ በሚኖሩባቸዉ አገሮች ዉስጥ ፌዴራሊዝም ግጭቶችንና ፍጥጫዎችን አስወግዶ ወይም አለዝቦ ልዩነትን ያቀፈ አንድነት መፍጠር የሚያስችል ፍቱን መድኃኒት ነዉ። ሆኖም ፌዴራሊዝም አስተማማኝ መድኃኒት የሚሆነዉ ለታማሚዋ ኢትዮጵያ በሚያስፈልጋት አይነትና መጠን በአዋቂዎች ሲታዘዝላት ብቻ ነዉ። አንድ መድኃኒት ሁሉንም በሽታ እንደማያድን ሁሉ ፌዴራሊዝምም መድኃኒት ነዉ እየተባለ ህዝብ ሳይሳተፍበት፤ ሳይጠናና በሽታዉን ማስወገድ በሚችልበት መልኩ ካልተዋቀረ ጭራሽ ህመሙን ያባብሰዋል እንጂ ፈዉስ አይሆንም። የቀድሞዋ ሶቭዬት ህብረትና ዩጎዝላቪያ ብትንትናቸዉ ወጥቶ ለአካባቢያቸዉ ሰላም መጥፋት ምክንያት የሆኑት ሁለቱ አገሮች ዉስጥ ፉዴራሊዝም የተፈጠረዉ ህዝብን በማስገደድና ጨፍልቆ አንድ በማድረግ በመሆኑ ነዉ። ዛሬም አገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ ፌዴራሊዝም ተገነባ ከተባለ ከሃያ ሁለት አመታት በኋላ የምናየዉ እንደዚህ አይነቱን አላዋቂዎች፤የአገር ጠላቶችና ዘረኞች የፈጠሩትን ዉስብስብ ችግር ነዉ።

ፌዴራሊዝም ኢትዮጵያ ዉስጥ በብሄር ብሄረሰቦች መካከል የሚታየዉን ችግር ዕልባት ሊሰጠዉ የሚችለዉ በአገሪቱ ብሄር ብሄረሰቦች መካከል የሚታየዉ ልዩነት የፖለቲካ ቅርጽና ይዘት ተሰጥቶት ህዝብ በዚህ ቅርጽና ይዘት ዙሪያ ግድግዳ ሰርቶ እራሱን ከሌሎች ነጥሎ እንዲኖር ሲደረግ አይደለም። ይልቁንም የፌዴራሊዝም ፍቱን መድኃኒትነት የሚረጋገጠዉ የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦች ልዩነታቸዉ የጥንካሬያቸዉ፤ የዉበታቸዉና የአንድነታቸዉ ምንጭ ሊሆን በሚችልበት መልኩ ሲደራጁና በክልል ካለማንም የበላይነት እራሳቸዉን ሲያስተዳድሩ በማዕከል ደግሞ ካለምንም ተፅዕኖ በጋራ ስልጣን ተከፋፍለዉ አገር መምራት ሲችሉ ብቻ ነዉ። ወያኔ የፈጠረዉ ፌዴራሊዝም ግን የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች በልዩነታቸዉ ላይ እንዲያተኩሩና ከራሳቸዉ ክልል ዉጭ ሌላ ምንም ነገር እንዳይመለከቱ ተደርጎ የተዋቀረ ፌዴራሊዝም በመሆኑ የአገሪቱ ብሄር በሄረሰቦች እራሳቸዉን አለማስተዳደራቸዉና በማዕከል ስልጣን አለመጋራታቸዉ ብቻ ሳይሆን አላስፈላጊ ወደሆኑ የእርስ በርስ ግጭቶች ዉስጥም እንዲገቡም ተደርገዋል።

የወያኔ ዘረኝነትና ከፋፍለህ ግዛ ፖለሲ ይዞት የመጣዉ አገራዊ ዉድቀት እርቃኑን ከታየባቸዉ ብዙ አጋጣሚዎች አንዱ በቅርቡ ባህር ዳር ላይ የተካሄደዉ 4ኛዉ የመላዉ ኢትዮጵያ የስፖርት ዉድድር ዝግጅት ነዉ። በዚህ የአገረቱን የተለያዩ ክልሎች ባቀፈዉ ዝግጅት ላይ ከሁለቱ የኢትዮጵያ ግዙፍ ብሄረሰቦች ማለትም ከአማራና ከኦሮሞ ብሄረሰቦች የመጡ ስፖርተኞችና ደጋፊዎቻቸዉ ከስድብና ተራ የቃላት መወራወር አልፈዉ የዱላና የቡጢ ዉርጅብኝ ሲለዋወጡ ታይተዋል። እዚህ ላይ አንድ እጅግ በጣም ያሳዘነን ነገር ቢኖር በአለማችን ላይ ለረጂም ግዜ አይንህን ላፈር ተባብለዉ የተራራቁ አገሮችና ህዝቦች ጥላቻቸዉንና በዉስጣቸዉ ያበጠዉን ቂምና በቀል ረስተዉ አንድ መድረክ ላይ እንዲተቃቀፉ የሚያደርጋቸዉ ኦሎምፒክንና የአለም ዋንጫን የመሳሰሉ የስፖርት ዉድድሮች ናቸዉ። አገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ ወያኔ የነሰነሰብን የዘረኝነት መርዝ ግን በአገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄድ የስፖርት ዉድድር ቀርቶ ኢትዮጵያ ዉስጥ በየቤተክርስትያኑና በየመስጊዱ ያለዉ ቄስ፤ ሼክና ፓስተር ተሰብስቦ በአንድ ላይ ቢጸልይም የፈጣሪ ግልጽ ጣልቃ ገብነት ካልታከለበት በቀር እንዲህ በቀላሉ የሚጠራ አይደለም። ወያኔ ይዞብን የመጣዉ የዘርኝኔት ጦስ እንደ ጉበት በሽታ ስር የሰደደና እንደ ካንሰር በፍጥነት በሰዉነት ዉስጥ የሚስፋፋ ክፉ በሽታ ነዉ።

ለመሆኑ የፍቅር መግለጫ መሆን፤ መቀራረብን መፍጠርና አገራዊ ስሜትን ማጎልበት የሚጠበቅበት ይህ አገራዊ የስፖርት ፌስቲቫል እንዴት ሆኖ ነዉ ወደ ኦሮሞና አማራ ብሄረሰቦች የቃላትና የጡንቻ ግብግብ ዘመቻ የተለወጠዉ? እነዚህ እጅ ለእጅ ተያይዘዉ ኢትዮጵያን ከወደቀችበት የጨለማ ማጥ ዉስጥ እጇን ይዘዉ ማዉጣት የሚገባቸዉ ግዙፍ ብሄረሰቦች ለምንድነዉ እንዲጣሉና አገሪቱን ጭራሽ ከድጡ ወደ ማጡ እንዲገፏት የሚደረገዉ?

ይህ ጥያቄ ሲያዩት ዉስብስብና ከባድ ሊመስል ይችላል፤ ሆኖም መልሱ ቀላል ነዉ። ወያኔ ኦሮሚያንና አማራን ጨምሮ መላዋን ኢትዮጵያ እየዘረፈ በሰላም መኖር የሚችለዉ በእነዚህ ሁለት የአገሪቱ ግዙፍ ብሄረሰቦች መከካል ሰላም ሲጠፉ ብቻ ነዉ። ይህ ደግሞ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ስንል የምንለዉ የቃላት አሉባልታ ሳይሆን በወያኔ የስልጣን ዘመን በግልጽ የታየና አሌ የማይባል ገሃዳዊ ሀቅ ነዉ። ለምሳሌ በሃያ ሦስቱ የወያኔ የስልጣን ዘመናት በግልጽ እንዳየነዉ ወያኔ ኦሮሞዉን ነፍጠኞች ሊመጡ ነዉ እያለ፤ አማራዉን ደግሞ የኦሮሞ ተገንጣዮች ሊበታትኑህ ነዉ እያለ አማራና ኦሮሞ በጠላትነት እንዲተያዩ አድርጓል። አገር ዉስጥና በዉጭ አገሮች የኦሮሞና የአማራ ኃይሎች ወደ ትብብር መድረክ ለመምጣት በሞከሩባቸዉ ግዜዎች ሁሉ ወያኔ ከፍተኛ ወጪ እያወጣ መድረኩ እንዳይካሄድ ወይም ትብብሮች ሲፈጠሩ የተፈጠሩት ትብብሮች ዕድሜ እንዳይኖራቸዉ አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪ ወያኔ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፤ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና በየክልሉ አማራዉና ኦሮሞዉ አይን ለአይን እንዳይተያይ የጥላቻ ግድግዳ ገንብቷል። ለምሳሌ በያዝነዉ ወር ሻኪሶ ዉስጥ ከዚህ ቀድም ተሰምቶ በማይታወቅ መልኩ የኦሮሞና የአማራ ተማሪዎች ጎራ ለይተዉ እንደተደባደቡና ግጭቱን ለማብረድ ወደ ስፍራዉ የተላካዉ ፌዴራል ፖሊስ ቁጥራቸዉ ለግዜዉ በዉል ያልታወቀ የኦሮሞ ተማሪዎችን ይዞ ማሰሩ ተሰምቷል። አብረዉ ጎን ለጎን ቁጭ ብለዉ ከመማርና ከመጫወት ዉጭ በአካልም ሆነ በስነ ልቦና ብስለት ለጋ የሆኑና የዘርና የጎሰ ግጭት ዉስጥ በፍጹም መግባት የሌለባቸዉ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አማራና ኦሮሞ ብለዉ ዘር ለይተዉ ሲደባደቡ ማየት አገራችን ዉስጥ ወያኔ የዘራዉ የዘር ፖለቲካ ምን ያህል ስር እንደሰደደ ሚያሳይ ተጨማሪ ማስረጃ ነዉ።

ወያኔ ኢትዮጵያ ዉስጥ ሰላም ሰፈነ፤ ብሄር ብሄረሰቦች መብታቸዉና እኩልነታቸዉ ተከበረ ብሎ በተናገረባቸዉ ባለፉት ሃያ ሁለት አመታት ዉስጥ የእነዚሁ ሰላም መጣላቸዉ በተባለላቸዉ ብሄር ብሄረሰቦች መካከል አያሌ ግጭቶች ተፈጥረዉ የብዙ ሠላማዊ ዜጎች ህይወት አለግዜዉ ተቀጥፏል፤ በብዙ ሚሊዮን ብር የሚቆጠር የደሃዉ ኢትዮጵያዊ ንብረት ወድሟል ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉ ዜጎች መጠለያ ፍለጋ ወደ ጎረቤት አገሮች ተሰድደዋል። እነዚህ ግጭቶች ደግሞ በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ አንዴ ወይም ሁለቴ ተከስተዉ የጠፉ ችግሮች ሳይሆኑ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች በተደጋጋሚ የተከሰቱ አደገኛ ግጭተች ናቸዉ። ለምሳሌ በኦሮሞና በአማራ፤ በኦሮሞና በሱማሌ፤ በቦረናና በጋሪ፤ በጉጂና በጌዲኦ፤ በሲዳማና በወላይታ፤ በሱማሌና በአፋር፤ በአማራና በጉሙዝ፤ በኦሮሞና በጉሙዝ ሀረር ዉስጥ በአሮሞ፤ በአደሬና በሱማሌ ብሄረሰቦች መካከል እያገረሹ የሚከሰቱት ግጭቶች የወያኔ ፌዴራሊዝም የፈጠራቸዉ ችግሮች አይነተኛ ምሳሌዎች ናቸዉ።

ኢትዮጵያ ዉስጥ በዬትኛዉም ክልል ለሚከሰቱ የጎሳ ግጭቶች ምክንያቱም ተጠያቂዉም ወያኔ ብቻ ነዉ። ይህንን ለማረጋገጥ ደግሞ በቂ ማስረጃዎች አሉ። ለምሳሌ ወያኔ ብሄር ብሄረሰቦችን አደራጅቶ የአገሪቱን ዘጠኝ የፌዴራል ክልሎች የገነባዉ ለክልል ምስረታ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆኑትን አኮኖሚያዊ፤ ባህላዊ፤ መልካምድራዊ፤ ታሪካዊ ፤ ስነልቦናዉና አስተዳደራዊ ግብአቶች ደፍጥጦ ዘርና ቋንቋን ብቻ መሰረት አድርጎ ነዉ። ይህ ዘርና ቋንቋን ብቻ መሰረት ያደረገዉ የክልል አደረጃጀት ደግሞ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች በድንበር፤ በሳር ግጦሽ፤ በማንነትና በቆየ ቂም በቀል እንዲጣሉና ደም እንዲፋሰሱ መንገድ ከፍቷል። ከዘህ በተጨማሪ ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ብሄረሰቦች ወደ ግጭት እያመሩ መሆናቸዉን ብዙ ቅድመ መረጃዎች ቢጠቁሙም ወያኔ አንድ ግዜም እንኳን ግጭት ከመጀመሩ በፊት የመከላከልና ተፋላሚዊአቹን ወገኖችች የማለዘብ እርምጃ ወስዶ አያዉቅም። በሦስተና ደረጃ ደግሞ ግጭቶች ከተፈጠሩና በሰዉ ህይወትና ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የወያኔ ፀጥታ ኃይሎች ህዝብን በመቀስቀስ ላይ የነበሩ የየአንድነት ፓርቲ አባላትን አሰሩ

አዲስ አበባ ዉስጥ በህጋዊ መንገድ የሰላማዊ ሠልፍ ቅስቀሳ በማድረግ ላይ የነበሩ የአንድነት ፓርቲ አባላት በወያኔ የጸጥታ ኃይሎች እየተለቀሙ ታስረዉ እስር ቤት መወርወራቸዉን የአዲስ አበባ መስተዳደር የአንድነት ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ሃለፊ ሆኑት አቶ ያሬድ አማረ ለኢትዮጵያ ሳቴላይት ቴሌቪዥንና ሬድዮ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ገለጹ። አቶ ያሬድ በዚሁ ጋዜጣዊ መግለጫቸዉ ጨምረዉ እንዳስረዱት በእርግጥ አቶ ሀብታሙ ታምሩ፣ አሸናፊ ጨመረዳ እና ደራሲ መቶ አለቃ አንዳርጌ መስፍን የተባሉ የፓርቲዉ አባላኢ የቅስቀሳ ወረቀቶችን ሲበትኑ በገ ወጥ መንገድ ታስረዋል ሆኖም ቅስቀሳው አሁንም በተሳካ በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ መሆኑን ነዉ ብለዋል።

ለገሃር ፖሊስ ጣቢያ አካባቢ ደግሞ አክሊሉ ሰይፉና ሰለሞን ጸሃየ መጠነኛ ድብደባ እንደተፈጸመባቸውም አቶ ያሬድ አማረ ገልጸዋል ። ታሪኬ ኬብና ኤፍሬም ሰለሞን በተባሉትም ላይ ሲቪል ለባሽ የደህንነት ሰራተኞች ሊመቱዋቸው ሲሞክሩ ህዝቡ መብታቸው ነው በሚል ተከላክሎላቸዋል። የአዲስ አበባገድ መስተዳደር የሰላማዊ ሰልፍ ክፍል አንድነት ፓርቲ ላቀረባቸው የተለያዩ አማራጭ የመሰለፊያ ቦታዎች ፈቃድ የከለከለ መሆኑን ቢገልጽም አቶ ያሬድ ግን ሰላማዊ ሰልፉ መጀመሪያ በተያያዘለት ቦታ ላይ ይካሄዳል ብለዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአንድነት ፓርተ የየአዲስ አበባ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ‹‹በህገ ወጥ መንገድ የሚቀለበስ ሰላማዊ የትግል ስልት ባለመኖሩ የአዲስ አበባ ህዝብ የወያኔ የተለከመደሰ ተራ ማስፈራሪያ ችላ ብሎ ለቀረበለት የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ ምላሹን እንዲሰጥ ጠይቋል።የሰላማዊ ሰልፍ ማሳወቂያ ክፍል ህገ ወጥ ደብዳቤ በመጻፍ ሰልፉን ማከናወን አትችሉም ማለቱ ከህግ በላይ መሆኑን እንደሚያሳይ ፓርቲው ገልጿል። መጋቢት 28 ቀን 2006 ዓ.ም በአዲስ አበባ እንዲደረግ ቀጠሮ የተያዘለት ሰላማዊ ሰልፍ በተያዘለት ቀጠሮ እንደሚከናወንም ፓርቲው ግልጽ አድርጓል።

የእሪታ ቀን በሚል መሪቃል የሚካሄደው ተቃውሞ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችን በተለይም የውሃ፣ መብራት፣ ስልክና የትራንስፖርት ችግሮች እንዲቀረፉ ያለመ ነው። ህገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎችን እንዲያገለግል ኃላፊነት የተሰጠው አካል ህጋዊ እውቅና ካገኘ ተፎካካሪ ፓርቲ የሚቀርብለትን ደብዳቤ አልቀበልም ማለቱ ህገ ወጥ ተግባር በመሆኑ ግለሰቡ በመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ እንዲመሰረትባቸው ፓርቲው ወስኗል። ለህግና ህገ መንግሥታዊነት ጥብቅና ለመቆም ቃል የገቡት የፌዴራልና የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊሶች ህግን አክብሮ እየተንቀሳቀሰ ከሚገኘው ፓርቲው ጎን እንዲቆሙ ጥሪ ያቀረበው አንድነት፣ በሠላማዊ ሠልፍ ለሚደርስ ማናቸውም አይነት ኪሳራዎች፣ ጉዳቶችና መጉላላቶች ተጠያቂው ህጋዊ ቢሮ ይዞ ህገ ወጥ አሰራር የሚከተለው አካል መሆኑን ግልጽ አድርጓል። ፓርቲው በአቋም መግለጫው መጨረሻ የውሃ፣ የመብራት፣ የስልክ ችግር የመኖርና ያለመኖር ጥያቄ ከሆነ ውሎ ማደሩን በመግለጽ፤ የቅስቀሳ ስራውም ከዛሬ መጋቢት 24 ቀን 2006 ዓም ጀምሮ በይፋ እንደሚጀመር ግልጽ አድርጓል።

## ውሃ፣ መብራትና፣ቴሌ አሁንም የአዲስ አበባን ነዋሪ ሕዝቡን እንዳስመረሩት ነው

የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ መዲና መሆኗ የሚነገርላት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በመጠጥ ውሃ፤ በኤሌክትሪክ፤ በቴሌ አገልግሎትና በኢንተርኔት ሰርጭት እጥረት ክፉኛ በመሰቃየት ላይ መሆናቸወነ ብዙ የከተማዋ ነዋሪዎች ዝግጅት ክፈለቻን ድረስ ስልክ እየደወሉ በመናገር ላይ ናቸዉ። በተለይ በዚህ አመት የመብራት ኃይል፤ የሞባይልና የኢንተርኔት አገልግሎቶች መቆራረጥ እየባሰበት መምጣቱንና ግብር ከፋዩን ህበረተሰብ ለአላስፈላጊ ለሆነ ኪሳራ መዳረጋቸውን ለማወቅ ተችሏል። በያዝነው ወር የኤሌክትሪክ ኃይል ቢያንስ በሁለት ቀን አንድ ጊዜ ለሰዓታት የሚጠፋበት ሁኔታ በተደጋጋሚ መስተዋሉን ዘጋቢያችን ተዘዋውሮ ያነጋገርናቸው ነዋሪዎች የገለጹ ሲሆን በዚህም ምክንያት ለአንድ ፍሬ ሻማ ወጪ ከአራት እስከ አምስት ብር ለማውጣት ተገደዋል።

በተጨማሪም አንድ ጀሪካን የመጠጥ ውሃ በአንዳንድ አካባቢዎች እስከ10 ብር እየተጠየ መሆኑን የጠቀሱት ነዋሪዎች መንግስት በቴሌቪዥን የሚናገረውና በተግባር የሚታየው ሊጣጣም አልቻለም ይላሉ። በአዲስአበባ ቦሌ፣ ገርጂ፣ 22 ማዞሪያ፣ ፒያሳ፣ ሠንጋተራ የመሳሰሉ አካባቢዎችን ጨምሮ በብዙ የከተማው ክፍሎች ውሃ በተከታታይ ከአንድ እስከ አራት ቀናት የሚጠፋባቸው አካባቢዎች መበርከታቸውን የጠቀሱት ነዋሪዎች ሌሊት ሊመጣ ይችላል በሚል ብዙ ቤተሰቦች እንቅልፋቸውን በውሃ ጥበቃ ለማሳለፍ እየተገደዱ ነው ሲሉ አክለዋል። የወላጆችና የተማሪዎች ሥራና የትምህርት ጊዜያት በውሃ ጥበቃእየተስተጓጎለ መሆኑን አስረድተዋል።

የሞባይል አገልግሎትን በተመለከተ አንድ ሰው በቀላሉ ደውሎ ለማግኘት የኔትወርክ መጨናነቅ ማስቸገሩን፣ ኔት ወርክ ከተገኘም በኃላ ግንኙነት ላይ እያሉ በተደጋጋሚ የመቋረጥ ችግር እንደሚያጋጥም፣ ባልታወቀ ምክንያት የያዙት ሞባይል ኔትወርኩ ዜሮ ሆኖ ከአገልግሎት ውጪ የሚሆኑባቸው ቀናት መኖራቸውን አስተያየት ሰጪዎቹ አስታውሰዋል።

የኢንትርኔት አገልግሎትም በተመሳሳይ መልኩ የተዳከመ ሲሆን ጨርሶ ሚጠፋባቸው ቀናት መኖራቸውንም ጠቁመዋል።አስተያየት ሰጪያችን እንደተናጋሩት EVDO በመባል የሚታወቀው ቴሌ ፈጣን ነው የሚለው የአንተርኔት አገልግሎት ትላንት ሌሊት ተቋረጦ ከ12 ሰዓታት ቆይታ በኃላ መለቀቁን እንደምሳሌ አንስተው ለዚህ ዓይነቱ ችግር የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይቅርታ እንኳን ሲጠይቁ አለመስማታቸው ለሕዝብ ያላቸውን ንቀት የሚያሳይ ነው ብለዋል።

ጠ/ሚ ኃይለማርያም ደሳለኝ በቅርቡ በሰጡት መግለጫ 75 በመቶ የከተማው ክፍል 24 ሰዓታት ውሃ እንደሚያገኝ፣ ቴሌ የምትታለብ ላም መሆንዋን ቢገልጹም ይህ ግን ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት በተግባር አለመገለጹ እንዳሳዘናቸው ገልጸዋል። የውሃ፣የመስኖና ኢነርጂ ሚኒስትሩ አቶ አለማየሁ ተገኑ በጥር ወር መጨረሻ ለፓርላማው ባቀረቡት ሪፖርት በተለይ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ችግር የመልካም አስተዳደር ችግር አንድ መገለጫ ነው በማለት በይፋ ያመኑ ቢሆንም ችግሩን በፈጠሩት ወገኖች ላይ የተወሰደ እርምጃም ሆነ የተስተካከለ ነገር የለም።

## አዋሳ ዉስጥ በተማሪዎች መካከል ግጭት ተቀስቅሶ አንዳንድ ተማሪዎች ተጎድተዉ ሆስፒታል ገቡ

የደቡብ ክልል ዋና ከተማ የሆነችዉን አዋሳን ወደ ፌደራል መንግስት ለማዘዋወር የሚደረገዉን ሙከራ በመቃወምና ከቋንቋ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ባሳለፍነዉ ሳምንት አዋሳ ዉስጥ በአዛዙና በተማሪዎች መካከል በተቀሰቀወሰ ግጭት ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ተማሪዎች ቀላልና ከባድ ጉዳት እንደደረሰባቸዉ ከወደ ደቡብበክልል የሚደርሱን ዜናዎች አመለከቱ። በዚህ ለሰአታት በዘለቀዉና ከፍተኛ ዉጥረት በታየበት ግጭት የፌደራል ፖሊስ አባላት ከትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ የሚወጡ ተማሪዎችን ሲደበድቡ የታዩ ሲሆን፣ በውስጥ ያሉ ተማሪዎችም እንዲሁ ድንጋይ ሲወረውሩ መታየታቸውን የአይን እማኞች ገልጸዋል። በአካባቢዉ የነበሩ የአይን እማኞች በስልክ እንደተናገሩት የግጭቱን በፍጥነት ከቁጥጥር ዉጭ መሆን የተመከቱት የፌደራል ፖሊስ አባላት ጥይት በተደጋጋሚ በመተኮስ ታቦር ትምህርት እንዲዘጋ አድርገዋል።

አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ሰው ከግጭቶች ጀርባ የአካባቢው ባለስልጣናት እጅ አለበት ይላሉ።በተለይም አዋሳን ወደ ፌደራሉ መንግስት ለማዘዋወር በማሰብ አንዳንድ ቦታዎች ላይ የስም ለውጦች ማድረግ በመጀመሩ ግጭቱ እንደተነሳ የሚናገሩት ወገኖች፣ ተማሪዎች ያነሰዋቸው ጥያቄዎች በቀላሉ የሚፈቱ ሆነው ሳለ የመንግስት ባለስልጣናት ዝምታን መምረጣቸው ከግጭቱ ጀርባ እጃቸው እንዳለበት ያመላክታል ይላሉ።በሌላ በኩል ደግሞ ከማንነት ጋር በተያያዘ እየታየ ያለው ችግር ካለፉት 5 አመታት ጀምሮ እየተጠናከረ መምጣቱን የሚናገሩት አንዳንድ ነዋሪዎች፣ በተማሪዎች የተነሳው ግጭት ከቋንቋ ጋር ብቻ መታየት እንደሌለበትና ችግሩ ስር እየሰደደ የመጣ ጉዳይ መሆኑን በማስታወስ ያስጠነቀቅቃሉ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ እየታየ ለመጣው ከማንነትና ከጎሳ ጋር በተያያዘ ለሚፈጠሩ ችግሮች አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ከመጪው ምርጫ ጋር ሲያያይዙት ሌሎች ወገኖች ደግሞ ገዢው ፓርቲ የሚከተለው የብሄር ፖለቲካ አስከፊ ደረጃ ላይ እየደረሰ መሆኑን ያስጠነቅቃሉ።በባህርዳር በተደረገው የክልሎች የስፖርት ጨዋታ ላይ የስነምግባር ጉድለት መታየቱ፣ በጉጂና በቦረናዎች መካከል ግጭት መነሳቱ፣ በሻኪሶ በተነሳ ረብሻ ጉዳት መድረሱ ይታወቃል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**መካከኛ ሞገድ፡-** በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ፡-** በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፐሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ወያኔ እያለ በሰላም፤ እድገትና የህዝብ አንድነት ሊኖር

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ንብረት ላይ አደጋ ከደረሰ በኋላም ቢሆን ወያኔ ዬትኛዉንም አካል ለግጭቱ ተጠያቂ አድርጎ አያዉቅም። እነዚህ ሁሉ መረጃዎች የሚጠቁሙት ወያኔ የጎሳ ግጭቶች ምክንያት መሆኑን ብቻ ሳይሆን ግጭቶቹ እንዲፈጠሩ የሚጓጓ መሆኑን ነዉ።

አገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ የአማራዉ፤ የኦሮሞዉ የትግሬዉ፤ የሱማሌዉ፤ የሲዳማና የሌሎቹም ክልሎች ገበሬና ሰራተኛ ህዝብ አንዱ ከሌላዉ የሚፈልገዉ ወይም የሚጠብቀዉ ልዩ ጥቅምና ፍላጎት የለም። የአማራዉ ገበሬ ልክ እንደ ኦሮመዉ ገበሬ ፍላጎቱ የሚያርሰዉ የራሱ የሆነ መሬት ኖሮት አርሶ መብላት፤ ኑሮዉን ማሻሻልና በሰላም ልጆቹን ማሳደግ ነዉ። የኦሮሞ ገበሬ ይህንን የሰላምና የብልጽግና ፍላጎቱንና ህልሙን እንዳያይ ደንቃራ የሆነበት የአማራ ህዝብ አይደለም፤ ለአማራ ህዝብም ቢሆን ጠላቱ የኦሮሞ ህዝብ አይደለም። የኦሮሞዉ የአማራዉም ሆነ የሌሎቹ ብሄር ብሄረሰቦች ጠላት ወያኔ ነዉ። የኢትዮጵያ ህዝብ በሰላም ጎን ለጎን ተስማምቶ እንዳይኖር በነጋ በጠባ ሰላሙን የሚያደፈርሰዉና ህዝብ እርስ በርሱ በጠላትነት እንዲተያይ የሚያደርገዉ ወያኔ ነዉ። ኢትዮጵያ ገበሬ ከወያኔ ዉጭ ሌሎች የተሻሉ አማራጮችን እንዳይመለከት መሬቱን ቀምቶ ሲያሻዉ እነሱን አፈናቅሎ መሬታቸዉን ለባዕዳን የሚሰጠዉ አለዚያም መሬትን እንደ መደለያ መሳሪያ እየተጠቀመ የኤኮኖሚ ህይወታቸዉን ያደቀቀዉ ወያኔ ነዉ። ስለሆነም የኢትዮጵያ ህዝብ እርስ በርሱ ተከባብሮ ሰላሙን፤ ብልጽግናዉንና አንድነቱን አተጋግጦ ለመኖር ከፈለገ በመጀመሪያ የእድገቱ፤ የነጻነቱና የሰላሙ ጻር የሆነዉን ወያኔን ከጀርባዉ ላይ አሽንቀንጥሮ መጣል አለበት፤ ይህንን ለማድረግ ደግሞ ከዛሬ የተሻለ አጋጣሚ ሊመጣ አይችልምና ሁላችንም ክንዳችንን አስተባብረን በወያኔና በዘረኛ ስርዐቱ ላይ እንነሳ!!!

**ድል ለእትዮጵያ ህዝብ!**

## ሕወሃት የምርጫ ብድር እያደለ መሆኑ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ የሚከት እነደነበር የሚያስታውሱ ወገኖች የመመለሻ ጊዜው ለስሙ ሶስት ዓመት ይባል እንጅ የሚቀጥለው ዓመት ምርጫ እንደተጠናቀቀ የማስመለሱ ሂደት ወዲያውኑ ይቀጥላል ይላሉ።

ሕወሃት የተጎዱ የማሕበረሰብ ክፍሎችን መልሶ ለማቋቋም፣ እድገትን ለማፋጠን፣ ድርቅና ርሃብን ለመቀነስና ሌላም ሌላም እያለ ከዓለማቀፍ ማሕበረሰብ የሚሰበሰበውን የእርዳታ ገንዘብ የራሱን የጎጥ ቡድን አባላት ለመመልመል፣ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችን አባላትንና አጠቃላይ እንቅስቃሴያቸውን ለማቀብ እንዲሁም አንዳንድ ለፍትህ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የቆሙ ግለሰቦችን ለማፈን እንደሚጠቀምበት ይታወቃል።

ከዚህ በፊት በተለያዩ ጊዜያት በተመሳሳይ ሁኔታ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ለሚኖሩ አርሶ አደሮች ተሰጥቶ የነበረን ብድር በማስመለሱ ሂደት በተፈጠረ አለመግባባት ሕወሃት የቤት ጣራን ነቅሎ እስከመውሰድና የእርሻ በሬን በሃራጅ እስከማሸጥ የደረሰ ግፍ እንደፈጸመ የሚያስታውሱ ወገኖች ሰሞኑን በብድር ስም እየተረጨ ያለው የምርጫ ቅስቀሳ ገንዘብም መጨረሻው ከዚህ የተለየ እንደማይሆን ከወዲሁ ያስጠነቅቃሉ።

## የወያኔ ወታደሮች በቦዲ ብሄረሰብ አባላት ላይ

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ለማድረስና ለማከፋፈል ወደ ስፍራው ያቀናው ሾፌር ብርሃኑ ማሞ ከምሽቱ 1 ሰአት ላይ ሰውነቱን ወንዝ ዳር ቆሞ እየታጠበ ባለበት ጊዜ ማንነቱ ባልታወቀ ሰው በተተኮሰ ጥይት ተግደሎ አስከሬኑ አዋሳ ውስጥ ተልኮ ተቀብሯል።አካባቢው አሁንም በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ መሆኑን ድርጅቱ አክሎ ገልጿል።